12/25/08

በውጭ ሃገር ከሚኖሩ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን የተሰጠ የአቋም መግለጫ።

ይህ የአቋም መግለጫ በ12/09/08 በተለያዩ የዜና አውታሮችና በተለይም በአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ፤ የወያኔዋ አባል ታጋይ ርስተይ መብራህቱ፤ በውጭ ሃገር የወልቃይት ጠገዴ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን ወኪል ነኝ በማለት የሰጡትን ከእውነት የራቀ ቃለ መጠይቅ በተመለከተ ነው።

ወ/ሮ ርስተይ ለብዙ ዓመታት መሣሪያ አንስተው ከትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባር ጎን በመሰለፍ፥ በሕዝባቸው ላይ በደልና ወንጀል ድርጅታቸው ሲፈፅም፥ ከተባባሪነትና ተጠያቂነት ያልወጡ፣ እንዴት አሁን በደል፤ ስቃያና፤ ግፍ ሲፈጽሙበት የነበረውን ሕዝብ ወኪል ለመሆን ተነሱ? ጅራፍ ራሷ መትታ ትጮህለች እንዲሉ።

ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን፣ ወ/ሮ ርስተይና ጥቂት ተከታዮቻቸው እንደሚሉት ሳይሆን፣ እውነቱ ክዚህ እንድሚከተለው ነው። በ12/06/08 ስለ ወልቃይት ጠገዴ ጉዳይ ለመነጋገር በሚል ምክንያት፣ በወ/ሮ ርስተይ መብራህቱ አሳሳቢነት በ 3 ሰዎች ተባባሪነት ስብስባ መጠራቱና በስብሰባውም ብዙ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች እንዳልተሳተፉ በይፋ ታውቋል። ነገር ግን 27 ሰዎች መሳተፋቸውና፥ በተለያዩ ጉዳዮች ከተወያዩ በኃላ በተፈጠረው አለመግባባት፣ ጥቂት ግለሰቦች ስብሰባውን ረግጠው ሲወጡ፣ ቀሪዎቹ ግን 5 ሰዎች ያሉበት ኮሚቴ አቋቋመው መለያየታቸውና፣ ከተቋቋመው ኮሚቴም እራሱን ያገለለ ግለሰብ መኖሩም ለማረጋገጥ ተችሏል።

ውድ ወገኖቻችን፣ ከስድስት ዓመት በፊት ማለት በወርሃ መስከረም 2002 በውጭ ሃገር ያሉ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን በኮሎምቦስ ኦሃዮ (በሃገረ አሜሪካ) ታላቅ ኮንፍረንስ አዘጋጅተው፤ ወያኔ በኢትዮጵያ በተለይም በወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ላይ የፈፀመችውና በመፈጸም ላይ ያለችውን ወንጀል፣

- አንድን ወገን አጥፍቶ በሌላ የመተካት
- በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወገኖች በአሰቃቂ ሁኔታ የመግደል
- በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ንፁሃን አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እስር ቤት ውስጥ እንዲማቅቁ የማድረግ
- ብዙ ሴቶች እህቶቻችን ለአቅመ ሔዋን እንኳ ያልደረሱ አስገድዶ የመድፈር
- የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ በባህሉ፣ በቋንቋው እንዲያፍርና የስነልቦና ኪሳራ እንዲደርስበት ያላሰለስ ጥረት የማድረግ
- የአካባቢውን ተወላጅ ለም ከሆነው መሬቱ በማፈናቀልና ለስደት በመዳረግ፣ በምትኩ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች ብቻ አምጥቶ የማስፈር ( ሑመራ፣ አዲጉሹ፣ ዳንሻና የመሳሰሉት 99.9% የትግራይ ተወላጆች ብቻ እንዲሰፍሩ የማድረጉ)
- ቤቱንና ንብረቱን በመዝረፍ በድህነት እንዲማቅቅ፣
- ስብዓዊ መብቱና ነፃነቱ ተገፎ፣ በተወለደበትና ባደገበት ምድር ላይ ሁለተኛ ዜጋ ሆኖ እንዲኖር የማደረግ፣ የመሳሰሉትን ከተመለከተና ከመረመረ በኋላ ጉዳዮን በቅርብ እየተከታተለ ለኢትዮጵያዊያን ወገኖቹም ሆነ ለዓለም ሕብረተሰብ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ አንድ ኮሚቴ አቋቋሚል።

ይህ ኮሚቴ (አካል) ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ ብዙ ጉዳዮችን አከናውኗል እያከናወነም ይገኛል። ለምሳሌ፣ በግፍና፣ በአሰቃቂ ሁኔታ የታሰሩትን ኢትዮጵያዊያን ወገኖች እንዲለቀቁ፣ አንድን ወገን አጥፍቶ በሌላ ለመተካት የሚካሄደው ዘመቻ እንዲቆም ወዘተ......የሚጠይቅ ግልጽ አቤቱታ ለጠቅላይ ሚኒስተሩ፣ ለፕረዚደንቱ፣ ለፍትህ ሚኒስተሩና ለፓርላማው በመላክ ኮፒውም ለአሜሪካ መንግሥትና ለዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ልኳል። በተለያዮ ጊዜያቶችም በተጨባጭ ጉዳዮች ላይ የተመረኮዙ ጽሑፎችን ለአገር ውስጥና ለውጭ የዜና አውታሮች በማቅረብ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአካባቢው እየደረሰ ያለውን ችግር አስከፊነት እንዲገነዘብ እያደረገ ይገኛል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ላለፉት 27 ዓመታት ወያኔ በዚህ ንፁሕ አገር ወዳድ ወገን ላይ ያለማቋረጥ እንደ እባብ ስትቀጠቅጥ፣ ስታሰቃይ፣ ዘግናኝ የሆነ ድርጊት ስትፈጽም ድምጻቸውን አሰምተው የማያውቁት የወ/ሮ ርስተይ ቡድን ዛሬ ድርጅታቸውን ደፍረው መለስተኛ ጥያቄዎች መጠየቃቸው በርቱ ቢያሰኝም፣ የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ መሰረታዊ ጥያቄ ግን፣ የህልውናና የመብት ጥያቄ እንጅ፣ የራስን በራስ ማስተዳደር፣ የአውሮፕላን ማረፊያና የኤሌክትሪክ ወዘተ..... የመሳሰሉ ጥቃቅን ችግሮች እንዳይደለ እግረመንገዱን እንዲገነዘቡልን እንፈልጋለን። ይልቁንስ በኛ እምነት በጋራ ልንጠይቃቸው ይገባል ብለን ያመንባቸው ጥያቄዎች <u>*ከብዙ በጥቂቱ*</u> ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።

1. ሃገር ቤት በግፍ በየእስር ቤቱ እየማቀቁ ያሉ፣ እንዲሁም ሕጋዊ ፍቃድ ተሰጥቷቸው በሱዳን ሃገር ሲኖሩ የነበሩና በ9/30/07 እየታደኑ ለወያኔ ታስረው የተሰጡት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን እንዲፈቱ
2. አንድን ወገን አጥፍቶ በሌላ የመተካቱ እኩይ ተግባር በአፋጣኝ ቆሞ፣ ይህንን ኢሰበአዊ ድርጊት የፈጽሙ የወያኔ ባለስልጣናትም በአስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡ
3. ከቀዮ የተፈናቀለው ወገን ወደ ቀደመ ቦታው ተመልሶ፣ ኑሮውን በሰላም እንዲመራ እንዲሆን
4. በተለያዩ ጊዜያቶች የተዘረፉት የሕዝብ ንብረቶች ተመልሶ፣ በአካባቢው ተወላጅ ወገኖች ላይ ለደረሰው የኢኮኖሚ ኪሳራ (በብዙ ቢሊዮን ብር የሚገመት) ካሣ እንዲከፈል።
5. ያለ ሕዝብ ፍላጎት የተደረገው ሕገወጥ ክለላ ተነስቶ፣ ወልቃይት ጠገዴ ወደ ነበረበት ወደ ጎንደር ክፍለ ሃገር እንዲቀላቀል
6. ለም የኢትዮጵያ መሬቶች ለስልጣን ማራዘሚያ ሲባል ለሱዳን መንግሥት ገጸበረከት መስጠቱ ቆሞ፣ በቅርቡ የተሰጠው ሰፊ መሬታችን በአፋጣኝ ይመለስ
7. የኢትዮጵያ ሕዝብ የስልጣን ባለቤትነት መብቱ ይከበር!!! ወዘተ......

ፍትህ፣ ነፃነት፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

ኢትዮጵያ በልጆቿ ኃይል አንድነቷንና ልዕልናዋን ታከብራለች!!